# የጎንደር ዞሪያ የመኢአድ ሰብስሳቢ:- አቶ አለምነህ ዋሴ  (ሸንቁጥ አየለ)

February 19, 2018

-ቪኦኤ እና እነ ኢሳት ለህዝብ ለማስተዋወቅ የሚሮጡት እነ አረጋዊ በርሄን እና እነ ገብሩ አስራትን ነዉ::
ለምን ?
አሁን ከተፈቱ እስረኞች ዉስጥ አንዱ የጎንደር ዞሪያ የመኢአድ ሰብስሳቢ የሆኑት አቶ አለምነህ ዋሴ አንዱ ናቸዉ:: በትናንትናው እለት ህዝቡ አቀባበል አድርጎላቸዋል::

አቶ አለምነህ ዋሴ ለዲሞክራሲ መስፈን ብዙ የታገሉ: በጽናት ለህዝባቸዉ ብልጽግና ደጋግመዉ የጮሁ: ስለህዝባቸዉ መበሳቀል አንባገነኖችን ሳይፈሩ ፊት ለፊት የታገሉ ጀግና ናቸዉ::

በትዉልድ ፍሰት ዉስጥ ብዙሃን ላይ የሚደርሰዉ ብሶት እና ግፍ እያስቆጫቸዉ የተመቾ ህይወታቸዉን ትተዉ ወደ ትግል የሚገቡ እዉንተኛ እና ቁርጠኛ ጀግኖችን በተገቢ መልክ መዘከር: መለዬት እና ማወቅ የህዝብ ሃላፊነት ቢሆንም ህዝብን በአግባቡ ሊያሳዉቀዉ የሚገባዉ ደግሞ ሚዲያዉ ነበር::

ሆኖም የኢትዮጵያ ህዝብ በሁሉ ነገር የተበደለ ነዉና ሚዲያ ተብዬዎቹ እነ ቪኦኤ እና እነ ኢሳት ለህዝብ ለማስተዋወቅ የሚሮጡት እነ አረጋዊ በርሄን እና እነ ገብሩ አስራትን ነዉ::
ለእነዚህ ሚዲያዎች የህዝብ ታጋይ እና ተቆርቋሪ ሆነዉ የሚታዩዋቸዉ የህዝብ ጠላት የሆኑት እና የኢትዮጵያን ህዝብ በጎሳ እንዲባላ ዋናዉን የመሰረት ድንጋይ የጣሉት እነ አረጋዊ በርሄ እንዲሁም እነ ገብሩ አስራት እንጅ እነ አለምነህ ዋሴ አይደሉም::

በእነዚህ ሚዲያዎች ፍልስፍና መሰረት ብዙ መስዋዕትነት የከፈሉት እነ አለምነህ ዋሴ: እነ ማሙሸት አማረ እና ሌሎችም የመኢአድ አናብስት ህዝ እንዲያዉቃቸዉ አያስፈልግም::
ከዚያ ይልቅ የህዝብ ደም እጃቸዉ ላይ ያለባቸዉ እነ አረጋዊ በርሄ እና እነ ገብሩ አስራት የህዝብ ተቆርቋሪ ተደርገዉ በእነዚህ ሚዲያዎች በስፋት እየቀረቡ እና እየተወደሱ ነዉ::
ለምን የሚለዉን በስፋት እመለስበታለሁ::

https://youtube.com/watch?v=t0ayDOTkXgk